የሰ/መ/ቁ.45545

መጋቢት 22 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሂሩት መለሰ

ብርሀኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ሸዋዬ ኑርዬ - ጠበቃ አቶ አበራ ማሬ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ምንአዩ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - ጠበቃ አቶ አበራ ታደሰ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ አመልካች ስላቀረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በከሳሽነት ቀርበው ሰኔ 24 ቀን 1998 ዓ.ም በተደረገ የእጅ በእጅ ሽያጭ ውል ብር 120,540.00(አንድ መቶ ሀያ ሺ አምስት መቶ አርባ ብር) ዋጋ ያለው የቢሮ ዕቃ ከተጠሪ(ተከሳሽ) ለመግዛት በመስማማት ብሩን ወዲያውኑ የከፈሉ መሆኑንና ተጠሪ ግን የገዛሁትን የቢሮ ዕቃ ወዲያውኑ አላስረከበኝም፡፡ ተጠሪ ዕቃውን ስላላስረከበኝ ከሃምሌ 1998 ጀምሮ ውሉን ማፍረሴን ለተከሳሽ አሳውቄአለሁ፡፡ ተጠሪ ገንዘቡን ሊመልስልኝ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ገንዘቡን ከነወለዱ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ ከከሳሽ (አመልካች) ጋር ያደረግሁት ውል የለም፡፡ ከሳሽ ያቀረቡት የእጅ በእጅ ሽያጭ የክፍያ ደረሰኝ ሰነድ ዕቃውን ሰነዱን የያዘው ሰው የተረከበበትን ቀን የሚገልፅ ስለሆነ ሰነዱ ዕቃውን ስለመረከባቸው በቂ አስረጅ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ሁለት ጭብጦችን መስርቷል፡፡ የመጀመሪያው በተጠሪና አመልካች መካከል የእጅ በእጅ ሽያጭ ተፈፅሟል ወይስ አልተፈፀመም? የሚል ሲሆን ሁለተኛው አመልካች ዕቃውን ተረክበዋል ወይስ አልተረከቡም? የሚሉ ናቸው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በተጠሪና በአመልካች መካከል የእጅ በእጅ ሽያጭ የተፈፀመ መሆኑን በቂ ማስረጃ አልቀረበም፣ የሽየጭ ውል አለ ቢባል እንኳን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2278(1) አመልካች ክፍያ ሲፈፅም ዕቃውን የሚረከብ መሆኑ ስለተደነገገና ይህንን በምስክር ማስተባበል ስለማይቻል ከሳሽ(አመልካች) ያቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤት የሽያጭ ውል የለም በማለት የወሰነው እኔ ባቀረብኩት ሰነድ ስም አልተጠቀሰም በማለት ነው፡፡ ሆኖም እኔ ያቀረብኩት ክፍያ የፈፀምኩበት ደረሰኝ ነው፡፡ የማይንቀሣቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በፅሑፍ እንዲደረግ ህግ አያስገድድም፡፡ እኔ ደረሰኙን ይዤ መገኘቴ ከተጠሪ ጋር የዕቃ ግዥ የፈፀምኩ መሆኑን የሚያስረዳ ደጋፊ ማስረጃ ነው፡፡ ተጠሪ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2278

ዕቃውን አላስረከበኝም። ተጠሪ የሸጠውን ዕቃ የሚያስረክብበት የራሱ ሥርዓት ያለው ሲሆን በዚያ ሥርዓት መሠረት ዕቃውን ስለማስረከቡ አላስረዳም። በእኔ በኩል ተጠሪ የገዛሁትን ዕቃ ለማስረከብ የቆጠርኳቸውን ምስክሮች ለማስረዳት ያቀረብኩትን ጥያቄ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2278 እና ፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2006 የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት ውሉ እንዲፈርስና ወደ ነበርንበት እንድንመለስ አለመወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል።

ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የያዙት ደረሰኝ ተጨማሪ እሴት ታክስ የተከፈለበት ደረሰኝ እንጅ የሽያጭ ውል መኖሩን የሚያስረዳ አይደለም። ፍርድ ቤቱ ለፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2278(1) የሰጠው ትርጉም ስህተት የለበትም። ድርጅታችን በመጋዘን የሌለን ዕቃ እና ወዲያውኑ የማናስረክበውን ዕቃ ዋጋ የመቀበል ልምድ የለውም። አመልካች ውሉ እንዲፈርስ ከሀያ ስምንት ቀናት በኋላ መሆኑ ውሉን አጠራጣሪ ያደርገዋል የሚል ክርክር አቀርቧል። አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል።

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል። ጉዳዩን እንደመረመርነው የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ፍርድ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

ከመዝገቡ ለመረዳት እንደቻልነው አመልካች የቢሮ ዕቃ ከተጠሪ የገዙ መሆኑን የዕቃውን ዋጋ ገቢ ያደረጉ መሆኑንና ዕቃውን ከተጠሪ ተረክበው ያልወሰዱ መሆኑን ለማስረዳት የፅሑፍ (የሰነድ) ማስረጃና የሰው ምስክሮች ዘርዝረው አቅርበዋል። የሥር ፍርድ ቤት የእጅ በእጅ ሽያጭ ውል በማለት ውሣኔ የሰጠው ተጠሪ ለአመልካች የቢሮ ዕቃ የሸጠ መሆኑን ለሽያጭ ውል በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2266 በተሰጠው ትርጉም መሠረት አመልካች ለማስረዳት ያቀረቧቸውን ሁሉንም ማስረጃዎች በመመርመርና በመመዘን ሣይሆን አመልካች በሰነዱ ማስረጃነት ያቀረቡትን የዕቃ ዋጋ የተከፈለበትና የተጠሪ ተጨማሪ እሴት ታክስ የሰበሰበ መሆኑን የሚያረጋግጠውን ከአመልካች እጅ የሚገኘውን ደረሰኝ ብቻ በመመርመር ነው። የሥር ፍርድ ቤት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የቢሮ ዕቃ ሽያጭ ውል አለ ወይስ የለም? የሚለውን ጭብጥ የወሰነው ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን በአመልካች በኩል የቀረቡ ማስረጃዎችን በመስማትና በመመርመር አለመሆኑ ከፍተኛ የሆነ የዳኝነት አካሄድ ሥርዓት ጉድለት የፈፀመ መሆኑን የሚያመለክት ሆኖ አግኝተነዋል።

በሌላ በኩል የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረቡት ደረሰኝ የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2278(1) የተሸጠውን ዕቃ ማስረከብ ከዋጋው መከፈል ጋር አንድ ላይ መሆን እንዳለበት ስለሚደነግግ አመልካች ገንዘብ በተቀበለበት ጊዜ ዕቃዎቹን መረከቡን ደረሰኙ ያስረዳል ሌላ ማስረጃ መሰማት አይቻልም በማለት የሰጠው የሕግ ትርጉም ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም። የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2278 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ቃል በቃል ሲነበብ "በውሉ የተነገረ ተቃራኒ ነገር ከሌለ በቀር የተሸጠውን ማስረከብ ከዋጋው መከፈል ጋር በአንድ ጊዜ መሆን አለበት" የሚል ነው ይህ ድንጋጌ በሻጭ ላይ ግዴታ የሚጥል ድንጋጌ ነው። የእጅ በእጅ ሽያጭ በሆነ ጊዜ የዕቃው ዋጋ ሲከፈል የተገዛውን ንብረት ወዲያውኑ ለገዥ የማስረከብ ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል። የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2278 ንዑስ አንቀፅ 2 ሻጭ ዕቃውን ለገዥ ሣያስረክብ ሊቆይ የሚችልበትን ልዩ ሁኔታ ይደነግጋል።

የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2278 ንዑስ አንቀፅ 1 በተደነገገው መሠረት ገዥ ገንዘቡን ከከፈለ ከግማሽ ሠዓት በኋላ ከሶስት ሠዓት በኋላ ወይም በማግስቱ ለመረከብ ተስማምቶ የነበረ መሆኑን በማናቸውም አይነት ማስረጃ ሊያስረዳ የሚችል ስለመሆኑ "በውሉ የተነገረ ተቃራኒ ቃል ከሌለ በቀር" ከሚለው የድንጋጌው ሐረግ ለመረዳት እንችላለን። ከዚህ በተጨማሪ ገዥ የዕቃውን ዋጋ ሙሉ በሙሉ የከፈለ ቢሆንም ሻጭ ዕቃውን ወዲያውኑ በማስረከብ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2278 ንዑስ አንቀፅ 1 የተጣለበትን ግዴታና ኃላፊነት ያልተወጣ መሆኑን ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ማስረጃ በማቅረብ የማስረዳትን መብቱን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2278 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ የሚገድብ አይደለም። ከላይ የተገለፁትን ሁኔታዎች በማስረጃ በማረጋገጥ ገዥ የዕቃውን ዋጋ ለሻጭ ከፍሎ ዕቃውን ያልተረከበ መሆኑን በማስረዳት ሻጭ ዕቃውን እንዲያስረክበው ወይም የሽያጭ ውሉ ፈርሶ ገንዘቡን እንዲመልስለት መጠየቅ የሚችል መሆኑን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2278 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ የማይገደብ ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ የዕቃውን ዋጋ ከፍዬ ዕቃውን አለመረከቤን በማስረጃ

ላረጋግጥ በማለት ያቀረበውን ጥያቄ ለህጉ ድንጋጌ የተሟሟተ ትርጉም በመስጠት ዕቃውን አለመረከብህን በማስረጃ ለማረጋገጥ አትችልም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛው ፍርድ ቤት ከላይ የተገለፀው የዳኝነት አካሄድ ግድፈትና የህግ አተረጓጎም ስህተት ያለበትን ውሣኔ ሣያርም ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሣኔና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ተሸሯል፡፡
2. የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካች ከተጠሪ ጋር የቢሮ ዕቃዎች ለማግዛት ውል የተዋዋለ መሆኑን፣ አመልካች ለዕቃዎቹ ክፍያ የፈፀመ መሆኑን ወይም አለመሆኑንና አመልካች ዕቃዎቹን ተረክቦ የወሰደ መሆኑን ወይም አለመሆኑን በአመልካችና በተጠሪ በኩል የሚቀርቡለትን አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች በመስማትና በመመርመር ውሣኔ እንዲሰጥ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343(1) መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ